## 6. የዓለም አቀፍ እርዳታና የእርዳታ ድርጅቶች ሚና በሽግግር ወቅት

### 6. 1. የኩርዲስታን ምሳሌ

በአቶ ኬንደል ኔዛን፣ የኩርድ ኢንስቲትዩት ፕሬዝዳንት
ፓሪስ

በመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ተሰበጣጥሮ የሚኖረው የኩርድ ህዝብ ቁጥር 25 ሚሊዮን ይገመታል:: 12 ሚሊዮን በቱርክ፣ 2 ሚሊዮን በኢራን፣ 4.5 ሚሊዮን በኢራክ 1 ሚሊዮን ደግሞ በሶርያ ይኖራሉ:: በተጨማሪም በሶቭየት ህብረት የኩርዶች ማህበረሰብ ሲገኝ በምእራብ አውሮጳ በስደት የሚገኙ ደግሞ 650 ሺህ ይገመታሉ:: ኩርዶች በመካከለኛው ምሥራቅ ነባር ከሚባሉት ህዝቦች የሚቆጠሩ ናቸው::

ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በኋላ የኦቶማን ኢምፓየር ሲፈርስ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች የመካከለኛ ምሥራቅ አገሮችን ሲከፋፍሉ ኩርዲስታንን በቱርክ፣ ኢራክ፣ ኢራንና ሶሪያ መካከል አከፋፈሏት:: እንዲህ ዓይነቱ ግፍ የተፈጸመው ከኩርዲስታን ህዝብ 90% በላይ አንድነቱን ጠብቆ የራሱ መንግሥት ለማቋቋም ፍላጎት እንደነበረው በግልጽ እየታወቀ ነበር::

በተለያዩት ሀገሮች ተሰበጣጥሮ የሚገኘው የኩርድ ህዝብ ይህንን ግፍ በመቃወም ገና ከመጀመሪያው አንስቶ ታግሏል:: በተለይ ከ1961 በኋላ የኢራክ መንግሥት በግዛቱ ውስጥ የሚገኙት ኩርዶች ላይ የአረብነት ባህል ለመጫን የአወጣውን እቅድ ከሥራ ላይ ማዋል ስለጀመረ የኩርድ ህዝብ ለትጥቅ ትግል ተነሳ:: በኢራን በተለይ የእስላማዊው አብዮት ከተደረገ በኋላ የኩርድ ህዝብ ለራሱ ሪጂናል አውቶኖሚ ለጠየቀው ለኢራን ህዝብ ደግሞ የብዙ ፓርቲዎች ዲሞክራሲ ጠይቆ ተንቀሳቀሰ::

እንግዲህ በዚህ ሁኔታ የእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ሚና ምን ሊሆን ይችላል? ኩርዲስታን የባህር በር የሌላትና የህዝቧን የዲሞክራሲ ጥያቄ በሚቃወሙ ሃገሮች የተከበበች አገር ነች:: የውጭ ጋዜጠኞች እንደ ልብ የማይደርሱበት አከባቢ በመሆኑ የኩርዲስታን ጉዳይ በዓለም አቀፍ ሚዲያ ብዙ ጊዜ አይነሳም:: በዛሬው ዓለም ደግሞ ጋዜጣ፣ ራዲዮና ቲቪ የረሳው ህዝብና አገር ዱፍን ዓለም የረሳው ህዝብና አገር ነው::

ነገሮችን ለመቀየር የረዳው በኢራክና ከኢራን መካከል የተነሳው ጦርነት ነበር:: ሁለቱም አገሮች ርዳታ ሰጭ ድርጅቶች እየጋበዙ ሌላው በሃገሩ ውስጥ በሚገኙ የኩርዲስታን ህዝቦች ላይ የሚፈጸመውን ግፍ ለማጋለጥ መሯሯጥ ጀመሩ:: ይሁም ሆኖ እስከ 1988 ዓ.ም. ድረስ ጋዜጠኞች አልደረሱለንም:: በዚህ ሁኔታ እርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ትልቅ ችግር ላይ ወደቁ:: በየደረሱበት በኩርድ ህዝብ ላይ የሚፈጸመውን ግፍ ይታዘባሉ:: ያላቸው ምርጫ ወይ አይተው እንዳላዩ ሆነው ሥራቸውን መቀጠል ወይ ደግሞ ይህንን ሁኔታ ለውጭው ዓለም ማጋለጥና ሥራቸውን አቋርጠው መባረር ነበር::

በ1988 ዓ.ም. ለአስራ አምስተኛ ጊዜ ኢራክ የኩርዲስቶቹን መንደሮች በመርዝ ጢስና በጋዝ አጠቃች:: በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ 5000 ሰዎች ተገደሉ:: ለኢራን ይሄ ጥሩ አጋጣሚ ነበር የሸውም ጋዜጠኞችን በሰፊው በመጋበዝ ይሄ ግፍ ለውጭው ዓለም እንዲጋለጥ ፈቀደች:: የዓለም ህዝብ ቁጣ ተቀሰቀሰ:: ግን አሁንም ቢሆን የውጭ መንግሥታት የኢራክን አገዛዝ መደገፋቸውን ቀጠሉ:: ምክንያቱም በዚያን ጊዜ የኢራክ መንግሥት የሺአይት እስላሞችን የመስፋፋት አደጋ መከቶ የያዘ መንግሥት ነው ተብሎ ይገመት ስለነበር ነው::

በዚህ ሁኔታ የእርዳታ ሰጭ ድርጅቶችና የኩርድ ስደተኞች ጩኸትና አቤቱታ ምንም ሰሚ አላገኘም፡፡ ለምሳሌ ያህል በዚህ በተቀሰቀሰው የዓለም ህዝብ ቁጣ በመገፋፋት የአሜሪካ ሴኔት በኢራክ ላይ እቀባ እንዲደረግ ወሰነ፡፡ ግን አስተዳደሩ እንኳን ይህን የቅጣት ውሳኔ ከሥራ ላይ ሊያውል ቀርቶ ለኢራክ የአንድ ቢሊዮን ደላር ተጨማሪ ብድር ፈቀደ፡፡ ይኸ የሚያሳየው በእንደዚህ ዓይነቱ የመንግሥታት ጥቅም በሚያይልበት ሁኔታ የእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ሚና እስከ ዚህም አጥጋቢ ውጤት ለመስጠት እንደማይችል ነው፡፡ ይህ ደግሞ በኩርዲስታን ብቻ ሳይሆን በካምቦዲያም የታየ ነው፡፡

ግን ደግሞ ትንሽ ቆየት ሁኔታው ተቀየረ፡፡ የፐርሺያን ገልፍ ጦርነት መጣ፡፡ሁኔታውን በቅርብ በመከታተል የዓለም ጋዜጠኞች ወደ አካባቢው ጎረፉ፡፡ በጦርነቱና በሚደርስባቸው ጭፍጨፋ የተነሳ ወደ ጎረቤት አገሮች በመጉረፍ ላይ ያሉት ከ2 እስከ 3 ሚሊዮን የሚገመቱ የኢራክ ኩርዶች ከፍተኛ ትኩረት አገኙ፡፡ በዚህም ሳቢያ እርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ከዓለም ህዝብ ብዙ ገንዘብ መሰብሰብ በመቻላቸው በሺህ የሚቆጠር ሕይወት ለማዳን ችለዋል፡፡ ይህም ሆኖ የችግሩ ብዛት ይህ ነው የማይባል ስለነበር፣ እርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ብቻቸውን ሊወጡት የሚችሉት አልነበረም፡፡ስለዚህም መንግሥታት በዚህ ጥረት ለመሳተፍ ተገደዱ፡፡

በዚህ ሳቢያ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ የተባበሩት መንግሥታት "ጣልቃ የመግባት መብት" የሚለውን ሃሳብ ያጸደቀው፡፡ በዚህ የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ በመጠቀም የአሜሪካን፣ የእንግሊዝና የፈረንሳይ ሠራዊቶች በመጨፍጨፍ ላይ ሳለው የኩርድ ህዝብ እርዳታ በመለገስ በየስደተኞች ሠፈር ተሰማሩ፡፡

ዛሬ በሽግግር ወቅት ላይ ነን ያለነው አብዛኛዎቹ ስደተኞች ወደእየአካባቢያቸው ተመልሰዋል የቀሩት ደግሞ በየስደተኛ መጠለያዎች ሆነው ለኩርዲስታን ችግር የፖለቲካ መፍትሄ እስኪገኝለት ይጠብቃሉ የሰብዓዊ እርዳታ በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ፡፡ ግን እንደህዝብ እንዳለ በአንድ ፈላጭ ቆራጭ ገዥ ግፍ ሲፈጸምበትና ከኑሮው ሲፈናቀል መፍትሄው ፖለቲካዊ ብቻ ነው ብለን እንገምታለን ፡፡ ይኸ ሲገኝ ብቻ ነው ርዳታ ሰጭ ድርጅቶች በኩርዲስታን ለሚደረገው የመልሶ መገንባት ጥረት አጥጋቢ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉት ፡፡

የኢራክ ኩርዲስታን የዚች አገር የእህል ጎተራና ዋና የከብት እርቢ አገር ነበረች ፡፡ በምግብ ራሷን የቻለች ነበረች ፡፡ ዛሬ 80% እህል ከውጭ የሚመጣ ነው ፡፡ ይህ ብቻውን የሚጠብቀን የመልሶ ገንባታ ሥራ ምን ያህል ከፍተኛና አስቸጋሪ እንደሆነ ይጠቁማል ፡፡ በዚህ ሁኔታ ርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ሊሰማሩ የሚችሉባቸው መስኮች ብዙ ናቸው ፡፡ መንገዶችን እንደገና መገንባት፣ ትምህርት ቤቶችን መልሶ ማቋቋም፣ እርሻ እንዲያንሰራራ ማድረግ፣ ከብት ርባታ እንደገና እንዲዳብር፣ የፋብሪካና የጎጆ ኢንዱስትሪዎች ሥራ ለሀገራችን ብልጽግና አስተዋጽኦ እንዲያደርግ... በእነዚህ መስኮች ሁሉ የርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ሚና ከፍተኛ ይሆናል ፡፡ እስካሁኑ ድረስ በውስጥ የህክምና እርዳታ በውጭ ደግሞ በባህል ተራድኦ ላይ አተኩረው ለነበሩት ርዳታ ሰጭ ድርጅቶች በመከፈት ላይ ያለው አዲስ የሥራ መስክ ነው ማለት ነው ፡፡

## 2. የሰሜን ርዳታ ሰጭ ድርጅቶችና የዲሞክራሲያዊ ሽግግር ጥያቄ

አቶ ክርስቲያን ለሽበሪ

በሰብዓዊ ርዳታ መስክ የሰሜን ርዳታ ሰጭ ድርጅቶች በሽግግር ዘመን ስላላቸው ሚና ሲወራ አንድ ነገር ማስታወስ ያስፈልጋል ፡፡ ብዙውን ጊዜ እነዚህ ድርጅቶች እንዲሠሩ

የሚጠየቁት ገና ግጭቶች ወይም ጦርነቶች ሙሉ በሙሉ ባላለቁበት ሁኔታ ነው ። እንደዚሁም በመሆኑ ሁለት ነገሮችን መለየት ያስፈልጋል ። እነዚህ ድርጅቶች ሥራቸውን ሲያካሄዱ ከተለያዩ የፖለቲካ ኃይሎች ማለትም ከመንግሥትም ወገን ከተቃዋሚውም ክፍል ለመገናኘትና አብሮ ለመስራት ይገደዳሉ ። ይህም ማለት ቀስ በቀስ በሀገሩ የውስጥ የፖለቲካ ግጭት ጠልቃ መግባትና ወገን ለይቶ መቆም ይመጣል ማለት ነው ። ሌላም ሁኔታ አለ ። በዓለም ደረጃ ብዙ ትኩረት የሚሰጠው አስቸኳይ ሁኔታ ሲመጣ በድንገት ወደአንድ አገር ስፍር ቁጥር የሌላቸው ርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ይጎርፋሉ ። እነዚህ ደግሞ ከሃገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች ጋር ምንም የረባ ግንኙነት የላቸውም ። የሀገሪቱን የተለየ ባህልና ታሪክ አያውቁም አብረው የሚሠሩትን ህዝብም አያውቁትም ። ይኸ ደግሞ የሥራቸውን ፍሬያማነት በጣም ውሱን ያደርገዋል ።

ከዚህ ተነስተን የምንለው አንድ ነገር አለ ። ርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ከፖለቲካ ውጭ ናቸው የሚለውን ተረት መቀበል ያስቸግረናል ። የግድ ፖለቲካ ውስጥ ይገባሉ ስለሆነም ሶስት ነጥቦችን ማንሳት ያስፈልጋል ።

1/ ከርዳታ ሰጭዎች በኩል ርዳታችን ምንም ወገናዊነት የለውም የሚለው አስተሳሰብ መቀረት አለበት ። በተለይ የጦርም ሆነ የፖለቲካ ግጭቶች ባሉበት አካባቢ በግልጽ ከማን ጋርና በምን የፖለቲካ ፕሮግራም ላይ ተመርኩዘው እንደሚሠሩ ማብራራት ይኖርባቸዋል ።

2/ የርዳታ ሰጭ ድርጅቶች አገር ውስጥ ያለው መንግሥትም ጉዳይ አለ ። ከጥቂት ዓመታት ወዲህ አንዳንድ የምዕራብ አገሮች በተለይ ደግሞ የፈረንሣይ መንግሥት እነዚህን ድርጅቶች መሣሪያ ለማድረግ ይጥራሉ ። ይኸ በጉልፍ ጦርነት ወቅት ከዚያም ቀደም ብሎ በካምቦዲያ ታይቷል ። በነዚህ አገሮች በተመከረው ሰብዓዊ ርዳታ ሳቢያ ዲፕሎማቲክ ዓላማዎችን ለማራመድ ሙከራ ተደርጓል ። በዚህ ጥያቄ ላይ በርዳታ ሰጭ ድርጅቶች በአንድ በኩልና በየሃገሩ መንግሥታትና በአውሮጳ ደረጃ ውይይትና ክርክር መካሄድ አስፈላጊ ነው ።

3/ በርዳታ ተቀባዩ አገር ያሉት የፖለቲካ ኃይሎች ጉዳይ ነው ። ከመንግሥትም ሆነ ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር አብሮ ለመሥራት ሲወሰን ይህ ትብብር የት ድረስ እንደሚሄድ ከመጀመሪያው ግልጽ ማድረግ ይጠቅማል ። በተለይ ጦርነት በሚካሄድበት ሁኔታ ከርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ጋር የሚሰሩት ኃይሎች የሰው ልጅ መብት የሚደፍሩበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል ። በዚህ ጊዜ ርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ሂሳዊ አስተያየትን የመስጠት መብታቸውን ማስከበር አለባቸው ። ይህ ሂሳዊ አስተያየት ወደ መለያየትና ሥራን ወደማቋረጥ የሚያመራም ቢሆን መፈራት የለበትም ።

ባለፉት 20 ወይም 30 ዓመታት የተደረጉት ሽግግሮች በጣም ግልጽ በሆነ ሁኔታ የተካሄዱ ስለነበሩ ብዙ ችግር አልፈጠሩም ። መጭው ጊዜ ግን አስቸጋሪ ይሆናል ብዬ እፈራለሁ ።

ባለፉት ዓመታት የተካሄዱት ሽግግሮች ብዙውን ጊዜ ሁለት ጥርት ያሉ ሠፈሮች የተጋጩባቸው ሽግግሮች ናቸው ። ቺሊና ፊሊፒንስ ለምሣሌ ምርጫ ለማድረግ ቀላል ነበር ። ዛሬ የምናያቸው ሽግግሮች ግን ውስብስቦች ናቸው ። ግጭቶቹ ሁሉ የሁለት ሠፈሮች ግጭቶች ሳይሆኑ

የተሰበጣጠረ ኃይሎች የሚፋለሙባቸው ሁነዋል ። ይህ ሁኔታ የርዳታ ሰጭ ድርጅቶችን ሥራ በተለያየ አጋጣሚ እንዲሰበጣጠር ያደርገዋል። በጉልፍ ጦርነት ጊዜ፣ በከምቦዲያ፣ በሶማሊያና በላይቤሪያ ያየነው ይኸንኑ ነው። እነዚህ ድርጅቶች ከገንዘብ አንጻር ሲታይ ለዚህ ችግር መፍትሄ መስጠት ይችሉ ይሆናል ግን በዚህ አንዱ ከሌላው ምን ያህል እንደሚሻል ባልተጣራ ሁኔታ ከተለያዩ የፖለቲካ ተዋንያን ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት በሃገር አቀፍ ደረጃ ስትራተጂ አውጥተው እንዳይሠሩ ያግዳቸዋል።

ሌላም አትኩሮ የሚጠየቅ ነጥብ አለ። ዛሬ እንደምናየው ከሆነ የርዳታ ሰጭ ሰብዓዊ ድርጅቶች ሚና ከሚገባው በላይ እየተጋነነ ሄዷል። ከአሥር ዓመት ወዲህ በብዙ ቦታዎች ያለው አስተሳሰብ እነዚህ ድርጅቶች የአንዱን አገር ማንኛውንም ችግር ሊፈቱ ይችላሉ የሚል ይመስላል። ስለዚህ በሦስተኛ ዓለም አገሮች አጉል ተስፋ እንዳይሰፍን የነዚህ ድርጅቶች ሚና ውሱን መሆኑን በሚገባ ማስረዳት ያስፈልጋል። የርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ሥራ እንደ ዋና መሣሪያ ሣይሆን እንደተቀጥላ መታየት አለበት።